# ድመት ብትመነኩስ

በየመድረኩ ላይ ፣ በገጠር ከተማ
የኢትዮጵያ ሱሴ ፣ ቅኝትን ያሰማ
ጀግና የተባለው ፣ አቀንቃኝ ቲም ለማ
ከውስጥ ተከናንቦ ፣ የጎጠኞች ሸማ
አመት ሳይቆጠር ፣ ከረፋና ገማ
ሱሴ ናት ያላትን ፣ አየነው ሲያደማ
የጎጥ አስተሳሰብ ፣ አይታይ ሲያለማ
የኋልዮሽ ጎታች ፣ ዓላማው ጨለማ ።

ኢያታቸው ኦነግ ፣ አባታቸው መለስ
የገበዩት ዕውቀት ፣ ስለ ጎጥ ፣ መቀደስ
የተማሩት ቢኖር ፣ አገር ማፈራረስ
ዛሬም የምናየው ፣ ምድሯ ስትታመስ
የማያውቁት ካባ ፣ አልብሶ ማወደስ
የዘቀጠ ዐይምሮ ፣ መቼም አይታደስ
የሚያውቁት እነሱ ፣ ፀብ መጫር ፣ መናከስ ።

በዲስኩር በወሬ ፣ የመረቀናችሁ
ስንኖር ፣ ኢትዮጵያዊ . . .
ስንሞት ፣ ኢትዮጵያ ፣ ስለተባችሁ
ኢትዮጵያ ፣ ሱሴ ናት ፣ ጠልፎ የጣላችሁ
እንዲያው በግርገር ፣ ለተሳከራችሁ
ለምርቃናው ጨብሲ ፣ እንዲሆንላችሁ
ጮሌ እያሳሳቀ ፣ ሲያፈናቅላችሁ
ሸገርን በኦሮሞ ፣ እያጠረላችሁ
አቢቹና ለማ ፣ አገር ሲያሳጡአችሁ
ጅብ ከሄደ ኋላ ፣ ትባንናላችሁ ።

ጭምብሉን አጥልቆ ፣ ሸፍጡን እያቦካ
በራሱ አጭር ቁመት ፣ ሁሉን እየለካ
በተንኮል በደባ ፣ ምኞቱን ሊያሳካ
ሚኒሊክ ቴዎድሮስን ፣ የኢትዮጵያን ዋርካ
በየመድረኩ ላይ ፣ ውዳሴ ትረካ
የሸፍጥ አረማመድ ፣ አሰልቺ መንቻካ
የአብይ እና ለማ ፣ ሸርክት ፖለቲካ
በትግሬዎች እግር ፣ ኦሮሞ እየተካ
ሲሳለቅ ያመሻል ፣ በኛ ላይ ሲያስካካ ።

እራሱን ዝቅ አርጎ ፣ የሚያምን በጎሳ
አዳርና ውሎው ፣ ከጎጠኞች ማሳ
ከተቀመጠበት ፣ መቼም አይነሳ
ተሻለው ስትለው ፣ ተመልሶ አንካሳ
ማለቃቀስ ብቻ ፣ ሌላውን ወቀሳ
ድመት ብትመነኩስ ፣ አመሏን አትረሳ
ዛሬም ተደገመ ፣ በለማ መገርሳ ።

ታዛቢው

March 2, 2019